# "ፈረንጅ አምላኩ..." ማን ነው? ፫ኛ

ገ/ኢ. ጐርፉ

ቀደም ብለን እንዳየነው 'የፈረንጅ አምልኮ' በሽታ በሆስፒታል ዘበኞችና በቤተ-መንግሥት አጋፋሪዎች ብቻ የተወሰነ ቢሆን ተመልክተን ማዘን፣ 'ባይማሩ ነው' ብለን በይቅርታና ምክር ማለፍ እንጂ እንዲህ በይፋ ጽፎ ማውጣት ባላስፈለገንም ነበር። ይህ በሽታ ግን በሃገራችን ከላይ እስከ ታች ተጋብቶ የተስፋፋ በመሆኑ በቀላሉ የሚታለፍ ጉዳይ እንዳልሆነ ቀጥሎ እናሳያለን።

እጅግ የሚደንቅ ሆኖ ያገኘነው ነገር በዩኒቨርሲቲና በመንግሥት ትብብር የወጣው የደሞዝ ሰነድ በውጭ ሃገር ሰዎችና በኢትዮጵያውያን መካከል ባለው ጉልህ የአድልዎ ልዩነት ነው። የማስትሬት ዲግሪ ላላቸው ኢትዮጵያውያን በ3,380 ብር ብቻ ሥራ ሲያስጀምሩ የውጭ ሃገር ሰዎችን ግን (ከህንድ፣ ከኤውሮጳ፣ ከአሜሪካ ለሚመጡ) በ$1,500 ያስጀምራሉ። ይህም ወደ አምስት ዕጥፍ የሚጠጋ የደሞዝ ልዩነት መኖሩን ያሳያል። የዶክቶር መዓረግ ላላቸው ኢትዮጵውያን ደግሞ በ4,000 ብር ሥራ ሲያስጀምሩ፣ ለውጭ ሃገር ሰው ግን በ$3,000 ማለትም የሰባት ጊዜ ዕጥፍ ደሞዝ ይሳጣል። ይህ ታድያ የፈረንጅ አምልኮ በሽታ ካልሆነ በቀር ምን ምክንያት ሊኖረው ይችላል?

ማንም ሰው ማውቅ የሚገባው፣ የውጭ ሃገር ሰው ወደ ሃገራችን ለሥራ የሚመጣው በሃገሩ ሊያገኘው ከሚችል ደሞዝ በጣም የበለጠ በማግኘቱ እንጂ ለጽድቅ አይደለም። (ይህ ግን በሚስዮን የኃይማኖት ሥራ ያሉትን አያካትት ይሆናል።) በኤውሮጳና በአሜሪካ ከ5% - 10% የሥራ አጥነት፣ በህንድ አገር ደግሞ እንደየቦታው ከ20% - 35% ከዚያም በላይ የሥራ አጥነት እንዳለ ይታወቃል። ለመሆኑ አገራችን በውድ ዋጋ የውጭን ሰዎች እየቀጠረች፣ የራስዋን ልጆች ግን በዝቅተኛ ዋጋ ቀጥራ መያዟ ለምንድነው? ታድያ የገዛ ልጆቿ ቢሸሿትና ውጭ ሃገር ቢሄዱ ምን ይደንቃል?

እንግዲያውስ ብዙ ኢትዮጵያውያን ምሁራን አገር ጥለው በመሄድ ከውጭ ሃገር በተለያዩ መስኮች ተሰማርተው የሚገኙት ዋና ምክንያቱ ይኸ ነው። የአዕምሮ ዝርፊያ (Brain Drain) ተብሎ ለሚነገርለት በሽታ፣ እስከ ዛሬም መፍትሔ ላልተገኘለት ችግር፣ መንግሥት ይህን የተዛባ የደሞዝ ሰነድ ቢያስተካክልና ቢያመቻች በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ባለሞያ ኢትዮጵያውያን ወደ ሃገራቸው ተመልሰው እንደሚመጡና እናት ሃገራቸውን እንደሚያገለግሉ፣ ብዙ ህንዶችና ሌሎች የውጭ ሃገር መምህራንና ሐኪሞችም ወደ ሃገራቸው እንደሚሄዱ ጥርጥር የለውም።

**ይቀጥላል...**